# ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)**
766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556   Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

## ግንቦት 97- የመብትና የዲሞክራሲ ትግላችን አሻራ

በግንቦት 1997 ዓ/ም ኢትዮጵያ ውስጥ የተካሄደው ህዝባዊ የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል ታሪክ ሁሌም ሲዘከር የሚኖርና አሻራ ጥሎ ያለፈ ነው:: መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፤ ከዚያ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ፤ በትግል ሂደቱ ላይ እምነት አሳድሮ ከዳር እስከ ዳር፤ የዘር፤ የሀይማኖት፤ የፆታ፤ የእድሜ የመሳሰሉት ልዩነቶች ሳይገድቡት፤ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ በሃሳብ አንድነት ተገናኝቶ፤ እጅ ለእጅ ተያይዞ በይቻላል መንፈስ እንደሱናሚ ተጥለቅልቋል:: ይህም በመሆኑ፤ ግንቦት 97 ከዓመት ዓመት ሲዘከር ይኖራል:: የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድርጅቶች ማህበር አባላትም ግንቦት 1997ን  የምናስታውሰው በልዩ ስሜትና ለወገናችን ያለንን አለኝታነት በማረጋገጥ ነው።

ሕዝባችን በከፋ የፖለቲካ አየር ውስጥ እየኖረ እንኳ በግልጽና በስውር እያካሄደ ያለው ትግል በስልጣን ላይ ላለው መንግሥት የጎን እሾህ ሆኖበታልና መብትና ነፃነት በሚከበርበት ዓለም የምንኖር ዜጎች ተጨማሪ ኃይልና ተጨማሪ ድምጽ ልንሆንለት ይገባል። ሥልጣን በመሣሪያ ኃይል የማሸጋገርን አደገኛ ልምድ በሠላማዊ የትግል ስልት እተካለሁ፤ የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍየ ዘላቂ መሠረት ያለው የዴሞክራሲ ሥርዓት እገነባለሁ ብሎ በአምባገነኖች እንግልት፤ ወከባ፤ ማሳደድ፤ እስርና ብሎም የጥይት ሰለባ መሆን ሳይገድበው በምርጫ ካርዱ አማካይነት ለገለጸው ወገናችን አለኝታ መሆናችንን፤ ይህን የታሪክ አጋጣሚ በመጠቀም በድጋሚ ለማረጋገጥ እንወዳለን:: ይህንንም አስመልክቶ ማሕበራችን በርካታ ፕሮግራሞች አዘጋጅቷል።

በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ካለፈው የትግል ዘመን የቀሰምናቸውን ልምዶች ካገናዘብን በኋላ ለቀጣዩ ዘመን የሚያስፈልገንን ዕቅድ ተልመናል። ከተመኘነው የውጤት ደርጃ ላይ ያልደረስነው የሠላማዊ ትግልን በርካታና ረቂቅ ሥልቶች በሥራ ላይ ለማዋል በቂ ትኩረት ባለመስጠታችንና በቂ ጊዜ ባለማግኘታችን እንደሆነም ተገንዝበናል። ስለሆነም የድርጅትና የአቅም ግንባታ ሥራን ተቀዳሚ ተግባር አድርገን በአመርቂ እንቅስቃሴ ውስጥ እንገኛለን። የማንኛውም ድርጅት ብስለት የሚለካው ያለፈውን ስህተት ላለመድገም በሚወስደው ርምጃና በጥሩው ልምድ ላይ ለመገንባት በሚያሳየው ጥረት ስለሆነ በአዲሱ ትልማችን ያለን ተስፋ የላቀ ነው።

ታሪካዊውን ግንቦት 7 የምናስታውሰው ሠላማዊ ትግሉን በሚያጠናክሩ፤ የሕዝብ አንድነትን በሚያጎለብቱ፤ የሀገር ቤቱንና የውጭውን እንቅስቃሴ በሚያስተሳስሩ ህዝባዊ ተሳትፎን በሚያጎለብቱ፤ የማስተማር፤ የማደራጀት፤ የሎቢ የዲፕሎማሲና የህዝብ ግኑኝነት እንቅስቃሴዎች ታጅበን ነው። በዚህ ረገድ በልዩ ልዩ የአሜሪካ ግዛቶች ውስጥ የሚከናወኑ ባለ ብዙ ዘርፍ ፕሮግራሞች ተነድፈው ሥራ ላይ መዋል ጀምረዋልና የሁላችንንም ተሳትፎ ይጠይቃሉ።

በአሁኑ ወቅት በመላ ኢትዮጵያ የተዘረጋው የአፈና ሥርዓትና የኤኮኖሚ ቀውስ ሀገሪቱን ለከፍተኛ አደጋ የሚዳርግ ስለሆነ ለሠላም፤ ለመብት ለዴሞክራሲና ለሀገር አንድነት የቆሙ ኃይሎች ሁሉ በተሀድሶ መንፈስ እጅ ለጅ ተያይዘው የሕዝባችንን ራዕይ እውን በሚያደርግ የጋራ ፕሮግራም ውስጥ እንዲሰለፉ ጥሪ እናስተላልፋለን።

ይህ የትግል ጥሪ፤ በተመሳሳይ መልኩ በመደራጀት ፤ ለህዝባዊ ትግሉ እጅግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ፤ በካናዳ፤ በአውሮፓ፤ በአውሰትራሊያ፤ በአፍሪካ፤ በሩቅ ምስራቅ መሃከለኛው ምስራቅና በኤስያ ለሚገኙ ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን በሙሉ ነው።

*መብትና ነፃነት የህዝብ የትግል ውጤቶች ናቸው !!!!*

**ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር**
**ኤፕሪል 23 ቀ 2008 ዓ/ም**